# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የፖለቲካ መረጃ ሥራ፣ መቅደላ - የድራማው የፍፃሜ ትዕይንት፣ ቴዎድሮስ ተኩስ ከፈቱ፣ የአቢሲኒያኖች ማጥቃት፣ የኮሎኔል ፔን የመጨረሻ ሰላምታ፣ ጅቦች ተከላዎችና ሥራቸው

ከደላንታ ሰሜን ጫፍ በኩል ተነስቶ እስከ ደቡቡ ዳርቻው ድረስ ያለውን ጉዞ ከመግለፃችን በፊት፣ ከእንጣሎ ከተነሳን ጀምሮ ካምፓችን ድረስ ስለመጣው የፖለቲካ ማዕበል ዕይታ እናድርግ። የመጨረሻው እኔ የጠቀስኩት ዜና፣ ቀኑ መጋቢት 6፣ 1868 ነበር።

መጋቢት 16 - ከራሳም የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፤ በውስጡም ቴዎድሮስ የእንግሊዞችን መምጣት ለወታደሮቻቸው መንገራቸውን ይጠቅስና፣ እንደ ቴዎድሮስ አገላለፅ፣ እንግሊዞች ነጋዴዎች ናቸው፤ ምንም እንኳን ጥሩ ነፍጥ ቢሠሩምና በርቀትም ቢጠቀሙበትም፣ ወኔ የጎደላቸውና በእጅ ለእጅ ጨበጣ ውጊያ ከአቢሲኒያውያን ጋራ አይወዳደሩም። ወታደሮቻቸው እንግሊዞችን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፏና እንደሚጨርሷቸው፣ የተማረከውን ንብረትም ወታደሮቹ መከፋፈል እንደሚችሉ ቃል ገብተውላቸዋል።[115]

መጋቢት 19 - በመንዚንጀር በኩል፣ የዋግሹም ጎበዜ ካምፕ እንደደረሰና በመስፍኑ በዋግሹም መልካም አቀባበል እንደተደረገለት ሰማን። በተጨማሪ ሲገልፅም፣ ጎበዜ ለሰር ሮበርት ናፒየር የወዳጅነት እጅ ዘርግቷል፤ ዘመቻውን ለማፋጠን ማድረግ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር በመልካም ፈቃድ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

ቴዎድሮስ በቤት ሆር ይገኛሉ፤ መድፎቻቸውን ከጀዳ ሸለቆ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። በመንገዳቸው አገሩን በሳት ለኩሰውታዋል። የዋድላ[116] ደላንታ ገዥ ሸፍቶ በንጉሡ ሠራዊትና በደላንታ ሰዎች መሀከል ጥቂት ግጭቶች ተፈጥረዋል።

---

115 በተቃራኒው፣ ቴዎድሮስ ለወታደሮቻቸው ስለንብረቱ ቢያወሩም፣ የእንግሊዝ ወታደሮችን ትክክለኛ ችሎታ ተናግረዋል። ይህን ሁኔታ ራሳም ራሱ በመፅሐፉ ያትታል።

116 የዋድላ ሰዎች የንጉሡን መምጣት ሲሰሙ ቤታቸውን ጥለው ወደ ላስታ ሸሽተዋል።

መጋቢት 20 - ሌላ መልክት ይደርሳል፡፡ ቴዎድሮስ የደላንታ አፋፍ ላይ ደርሰዋል፣ ወደ መቅደላ እየተጓዙ ነው፡፡[117]

መጋቢት 29 - የቃኘው ጦር አዛዥ ኮሎኔል ፋይሬ፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር ማስታወሻ ይልካል፤ በማስታወሻውም መንዚንጀር በቴዎድሮስ ቃፊር ወታደሮች መያዙን፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው በአምባቸውና በደላንታ መሀከል ያለውን የበሽሎን ወንዝ መልሰው እያቋረጡ እንደሆነ፣ ይህም እንግሊዞችን ለማሰፈራራት ታስቦ መሆኑን ይገልጣል፡፡

መጋቢት 31 - መንዚንጀር ከደጃች መሸሻ ካምፕ ሆኖ በራሱ በእጁ በተፃፈ ማስታወሻ፣ የጎበዜ ጄኔራል፣ ለር ሮበርት ናፒየር ሳንታሪ እንደደረሰ ሊገናኘው እንደሚመጣ ይጠቁማል፡፡ ቴዎድሮስ አዛው መቅደላ ናቸው፤ አምባው ከደረሱ በኋላ ተመልሰው በሽሎን[118] አላቋረጡም፡፡

ሚያዝያ 4 - በመጣው ዜና፣ የደላንታ ሰዎች ለቴዎድሮስ አሜን ብለው ገብረዋል፡፡

ሚያዝያ 8 - ራሳም ለኮሎኔል መርዌዘር ደብዳቤ ይልካል፡፡ ኮሎኔሉ ከጦሩ ጋራ፣ ከወልደ የሱስ ጋር ካደረገው የተሳካ ተልዕኮ እየተመለሰ ነው፡፡ የራሳም መልከት፣ "ተጠንቀቁ! ንጉሡ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ በሌሊት ጥቃት ሊያደርጉባችሁ ስለሚችሉ በጣም ተጠንቀቁ፡፡ ለኛ ስትሉ ከሰውየው ጋር በመልካም ሁኔታ ተደራደሩ፡፡ በትንሹም ቢሆን ቁጣቸው ከገነፈለ የህይወታችን መጨረሻ ይሆናል፡፡ በካምፓችሁ ጥሩ ሻምፓኝና መጠጦች አላችሁ ወይ? ውድ ኮሎኔል፣ ከአንተ ጋር በምገናኝበት ጊዜ የሚሆን ለኔም ጥቂት አቆይልኝ፡፡ ፈጣሪ ይባርክህ፡፡"

ሚያዝያ 9 ጠዋት፣ ሁለት ብርጌዶች ከጀዳ ሸለቆ በላይ ካለው ካምፓችን ተነሰተው ከመቅደላ ትይዩ ወደ ሆነው በደቡብ አቅጣጫ ወዳለው ሜዳ ተንቀሳቀሱ፡፡ ሜዳማ ቦታው እንደ ቢሊያርድ መጫወቻ ጠረጴዛ ለለላሳ የሆነና ስድስት ማይሎች ርቀት ያለው በመሆኑ፣ በሁለት ሰአታት ውስጥ ደቡብ ጫፍ ላይ ያለው አፋፍ ደረሰንና ካምፓችን መሰረትን፤ ቦታውም ቁልቁል ወደ በሽሎ ከሚወሰደው መንገድ ግማሽ ማይል ርቀት ነበር፡፡

አንባቢዎች ተከተሉኝ፣ በዚህ ደላንታ አፋፍ ጫፍ ላይ ሆኜ በተቻለኝ አቅም ሰመጥሩውን መቅደላና አካባቢውን ላሳያችሁ፡፡ አይናችሁን ግለጡና ዕይታውን ተመልከቱ!

---

117 እንግሊዞች፣ ለዳውንትና ለደላንታ አለቆች፣ ቴዎድሮስ መቅደላ እንዳይደርሱ እንዲቆርጧቸው መልከት ልከው ነበር፡፡ ያሰቡት አልሆነም፡፡ ቴዎድሮስ የዚህ መረጃ ደርሷቸው እንደሆን ማረጋገጫ የለም፡፡

118 የበጌምድር ደንበር እስከ በሽሎ ወንዝ ድረስ ነበር፡፡




*ወደ መቅደላ የሚወሰደው መንገድ*

ካለሁበት ከደልዳላው ሥፍራ ወደ ጠርዙ በኩል፣ ከቆምኩበት ሆኜ ቁልቁል ስመለከት፣ ቀጥ ያለ የሀምሳ ጫማ ጥልቀት ያለው የአለት ግድግዳ አለ:: ከዛም መቶ ጫማ ወይም ከዛ በላይ የሆነ ዳገታማ የሆነ እርከን ወደፊት ይዘረጋና፣ በድንገት በሌላ ቀጥ ባለ ተመሳሳይ ጥልቀት ባለው የአለት ግድግዳ ይቋረጣል:: ከስሩ በኩል ወደ መቶ ያርዶች ርዝመት ያለው፣ የተጥመዘመዘ፣



ከደላንታ አፋፍ፣ የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ



*ጉንጃቦቹ ሳንጃ ወድረው አቢሲኒያውያንን ሲያጠቁ*
William Barnes Wollen - the 1895 British book Illustrated

ለማግኘት በትግስት መጠባበቅ ጀመሩ:: ያን ያህል ሳይጠብቁ፣ ጠቆር ያሉት ሰዎች፣ ሰብሰብ ብለው ከጫካው መውጣት ጀመሩ:: ጉንጀቦቹም ተኩስ ከፈቱባቸው፤ እየተኮሱም፣ ከዳገቱ ቁልቁል ወደነሱ ይወርዱ ጀመር::



*የእንግሊዞች ሮኬት ተኳሾች ብርጌድ* (በእጃቸው የያዙት ቱቦ የሚመስል ነገር ሮኬት መተኮሻው ነው።) (From the collections of the Imperial War Museums)



የአሮጌ ውጊያ
(ዋቢ መፅሐፍት ተ.ቁ. 16)



(በዚህ ምስል፣ ሁለቱ ጋራዎች፣ ፋላና ሰላሴ ተለይተው ይታያሉ፤ ከፋላ ጋራ የሚታየው ጭስ የአፄ ቴዎድሮስ መድፎች ሲተኮሱ ነው።)

የምናርፍበት ቦታ ስንደርስ ድንኳኖቹ እንዳልመጡ አወቅን። እንኳን የሠራተኞች ጓዝ ሊደርስ ምንም ምግብም አልመጣም። ተከታዮች ግን በመቶዎቹ እየመጡ ነበር፤ እናም የተለያዩ ቃላት ለውጦች ሰደቦችና ወቀሳዎች መለዋወጥ ጀመሩ።

የተራቡ በቅሎዎቻ ማናፋት፣ ፈረሶችም ቢሆን የእህል ቀለባቸው ሰላልተሰጣቸው ማሰካካት ጀመሩ፤ ሆኖም፣ ለከብቶችም እህል ሆነ ለሰዎች ምግብም አልነበረም። የደከሙት ወታደሮችም መጡና አንዱ አንዱን ስለ ምግብ ይጠይቁ ጀመር። የተሠጣቸው መልስ እሉታዊ ነበር። እስከ እኩለ ሌሊት መቆየት እንዳለባቸው ተነገራቸው፤ ድንኳናቸውም ቢሆን እስከ ጠዋት ድረስ አይመጣም። ከዚህ በኋላ ጠንከር ያለ ከፍ ባለ ድምፅ ባይሆንም የመከፋት ጉርምርታ ተጀመረ።

"ለመምጣት ምንም እክል አልነበረም።" አሉ። "ለምንድን ነው ያልመጡት?" ለምን? እይ ሰው፣ ስህተት በየቦታ እየተሠራ ነው ወይ? ለምንድን ነው ሰህተት የሚኖረው? ለምን ሁሉም ነገር ሁልጊዜ ትክክል አይሆንም?

መኮንኖችን በሚመለከት፣ በተፈጥሮ የሚታየው በሁኔታው መንገሽገሽ፣ ሰራተኞቻቸው በየኮረጆቻቸው እንዲመገቡ ባመጡላቸው ቀለብ ምክንያት በረድ ብሏል። የሰዎች ሆድ ሊሞላና የምግብ ፍላጎት ሲረካ፣ በዚህ ቦታ እንደታየው ሁሉ፣ ወደ ጨዋታና መዝናናት ያመራሉ። በየሳቱ ዙሪያ፣ በቡድን ቡድን ተቀምጠው አዲሱ ውጊያና ትዕይንቶቹ ላይ የጋለ ውይይት ተደረገ።

እኩለ ሌሊት ሊሆን እብዛኛው ጓዝ መቷል፤ ነገር ግን ድንኳኖች ሊወጡ አልቻሉም፤ ለኛ የቀረው ነገር ወደሳቱና ወደ ጭሱ ጠጋ ብለን ባዶ ሜዳ ላይ መተኛት ነበር።

በካምፑ ዙሪያ፣ ብዛት ያላቸው ዘቦች እንዲቆሙ ተደረገ፤ ወታደሮቹ ለድንገተኛ ሁኔታ ተዘጋጅተው ሰመጠበቅ መሳሪያቸውን እንደታቀፉ ተኙ።

በምንጣፋችን ላይ ከመጠቅለላችን በፊት፣ የቀኑን ውሎ እያሰብን እያለን፣ ጆሯችን የዱር አውሬዎች ለመምጣታቸው መረጃ የሚሆን ድምፅ ያዳምጥ ጀመር። ረሃብ ያንሰፈሰፋቸው የጅብና የተኩላ መንጋ በዚህ ጨካኝ ጦርነት የወደቀላቸውን ድግስ ለመቦጫጨቅ መተዋል። እንግዳ የሆነ፣ በማታ ሰው ሰምቶት የማያውቀው አይነት፣ እንቅልፍ የሚያሰወስድ ዜማ እንቅልፍ እንዲወሰደን አደረገን፤ የደነዘዙት ጆሮቻችን በመጨረሻ የሰሙት ድምፅ ቢኖር፣ የተኩላዎችን የሚሰቀጥጥ ጩኸት፣ የጅቦችን ጉርምርታ፣ ጉጉቶች ከሚያሰሙት የሀዘን "ቱ- ዊት-ቱ-ዉ" ጋር ተቀላቅሎ ነበር።

# ምዕራፍ አስር

በውጊያው የተጎዱ ሰዎች፣ ጥሩ የለበሰ ምርኮኛ፣ የቴዎድሮስ ተስፋ መቁረጥ፣ ራሳም፣ ያልተጠበቀው እሰረኞችን መቀበል፣ የመጨረሻው የእጅ ስጥ ጥሪ

ከትላንትናው ማዕበላዊ ሜዳ በላይ፣ በዚህ አንግዳ በሆነ የሞቱና የሚሞቱ ሰዎች ባሉበት ሸለቆ በላይ፣ ከእንግሊዞቹ ካምፕ በላይ፣ እና ወደ ሰማይ በተዘረጉት የቋጥኞች ጫፎች በላይ፣ ፀሀይዋ በተለመደው የትሮፒክ ሙቀትና ብርሃን ማብራት ጀምራለች፤ ይህም፣ ሰው ባለቀበት የሰቅለት አርብ ማግሥት ነበር፡፡

ሰአት አብሳሪ ወፍ ከጫካው ውስጥ ከፍ ባለ ድምፅ ይጮሃል፤ በብሩህ ቀለሙ ሌላው ወፍ በደስታ ያፏጫል፤ ሌላውም ወፍ፣ ወደ ላይ ወደ ሰማይ ከፍ ብሎ በመንሳፈፍ ጣዕም ያለው ዜማ ያሰማል፤ ይህ ግን ወደ ህልም ከሚጎትተን ጉጉቶቹ ከሚያሰሙት የሻከረ ጩኸት ይለያል፡፡ የሠላም ከፍታዎች! የደስታ ሸለቆ፣ አይደለም ወይ?

በካምፑ፣ ወታደሮች አንደወትሯቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ፤ ሠላምታና ሆሚታዎችን ይቀያየራሉ፡፡

"ቾከራ ኢደር አኦ፣" *(አንተ ልጅ ና)* ጄኔራል ናፒየር ለአንድ ሂንዱስታን ሠራተኛ ሲናገር ሰማሁ፡፡ "ለሰርጀን[123] ሳሂብ ምስጋና ይገባዋል፣ ላየው እንደምፈልገው ሂድና ንገረው፡፡"

"ሰርጀን ሳሂብ መቷል፣" ቾከራው ሪፖርት አደረገ

"አሃ፣ ይሁን፡፡ ዶክተር እንደምን አደርክ፡፡ የሚያምር ቀን ነው፡፡ አይደለም እንዴ? ሪፖርትህን አዘጋጅተሃል?"

"አዎ፣ ሰር ሮበርት፣" ከኪሱ ወረቀት እያወጣ፣ ሰርጀኑ መልስ ሠጠ፡፡ "ይኸውና፣ ሰር! አንድ መኮንን ማለትም ካፒቴን ሮበርት እና ሰላሳ አንድ

123 የቀዶ ህክምና ሀኪሞች መጠሪያ

ወታደሮች ቆሰለዋል፤ ካፒቴን ሮበርትና ስምንት ወታደሮች በፀና የቆሰሉ ናቸው።።"

እዚህ ደረጃ ላይ ለማወቅ የነበረን ጉጉት መልስ አግኝቶ፣ ሁላችንም እንኳን ደስ ያለን ስሜት ተለዋወጥን። "እሰብ እንግዲህ፣ ወዳጄ፣ አንድ ሰው ሳይሞት ሰላሳ ሁለት ሰው ብቻ መቁሰል!" እንግዲህ በሌላው ወገን የደረሰውን ጉዳት እናረጋግጥ።

የአራተኛው አግረኛ ጦር ካፒቴን ሰዊኒ፣ ከእጃቢ ወታደሮች ጋር በጦር ሜዳ ቆሰለው የሚገኙ አቢሲኒያውያንን ወደ ካምፑ ሆስፒታል እንዲያመጣ ታዘዘ። እኔም አብሬው ሄድኩ። የሚያስፈራ ሁኔታ ነበር ለእይታችን የተከሰተው። የትናንትና ማታ ድምፅና ጩኸት ለዚህ ሰቆቃ ቢያዘጋጀኝም፣ በአውን ያየሁት ግን ካሰብኩት በእሰር እጥፍ ነው የነበረው። እራዊቶቹ እስከሬኖቹን ሲርመሰመሱባቸው አድረዋል። ከመጠን በላይ በተገኘው በዚህ የሰው አካል ፈስከውበታል፤ እንደሚባለው ከሆነ ድርቅ ሆኖም አያውቅም፤ ስለዚህ ብዛት ያላቸው ሥጋ በል አውሬዎች መቅደላ አካባቢ ነግሠውበታል፤ እነዚህ እራዊቶች ሀገሩን ከበሽታ ነው ያዳኑት። ከእሮጌ ውጊያ በኋላ ማታውኑ፣ ለአነሮች፣ ለተኩላና ለጅቦች፣ አግኝተው የማያውቁት ግብዣ ነው የቀረበላቸው።

የሙቱት ለዎች በጥንቃቄ ከተቆጠሩ በኋላ እዛው በወደቁበት ቦታ ተቀበሩ። በተጨማሪ ጥንቃቄ፣ የቆሰሉና ሌሊቱን በሙሉ በህመምና በሥቃይ ያደሩት፣ ከእራዊቶች መንጋጋ እንኳን ራሳቸውን በሙሉ ለመከላከል ያልቻሉት፣ በተገኘው መንገድ ወደ ሆስፒታል እንዲወሰዱ ተደረገ። ከሶስት ሰአታት ይህን ከመሰለ አድካሚ ሥራ በኋላ፣ የሚቀጥለው ሪፖርት ለዋናው ዕዝ ተሠጠ።

ሰባ እምስት የአቢሲኒያ ቁስለኞች ወደ ሆስፒታል ተወሰደዋል። 560 የሞቱ የጠላት ወታደሮች በቦታው በሰዎቹ ተቀብረዋል። በውጊያው ያለማሰለሰ ተከታታይ ጥቃት ያደርስ የነበረው የጦር መሪ፣ ደጃች ደረሰ፣ ከጉልበቱ በላይ በጥይት ተመትቶ አጥንቱ ስለተሰበረ በሸከም ወደ ሆስፒታሉ ተወሰደ። እንደሚባለው ከሆነ በካፒቴን ሰፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ጥይት ተመትቶ የወደቀው የፊታውራሪ ገብርዬ እስከሬን ማታውኑ በጄኔራል ናፒየር ትዛዝ ወደ መቅደላ ምሽግ ተልኳል። ይህም በዘመዶቹ እንዲቀበርና ቴዎድሮስ ከዋነኛ የጦር መሪና አማካሪያቸው ምርጡ እንደሞተ እንዲያዩ ነው።

ከቁርስ በኋላ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሰንደቅ እላማ በኩራት ከሰር ሮበርት ናፒየር ድንኳን በላይ ወደሚውለበለብበት ሥፍራ አመራሁ።

"ምን አዲስ ነገር አለ፣ ካፒቴን?" ብዬ የሰንቅና ትጥቅ ክፍሉን ረዳት አዛዥ ካፒቴን ሆላንድን ጠየቅሁት፡፡

"ምንም፤ ነገር ግን ጭምጭምታው፣ በካምፑ ወሰጥ የማይታመንና የማይረባ ወሬ ተሠራጭቷል ነው፡፡ እኔ ራሴ የማውቀው ነገር የለም፤ የማምነው፣ ሰር ሮበርት ቴዎድሮስ እጁን እንዲሰጥ ይጠይቃል፤ እና ከዛ በኋላ ጠላት ላይ እንደሚንቀሳቀስ ደፍሬ መናገር እችላለሁ፡፡" በማለት ካፒቴን ሆላንድ በቀላሉ መልሰ ሠጠ፡፡

ካፒቴን ሆላንድ በትክክል ነው የገመተው፡፡ ሰር ሮበርት ያቀደው ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ የሚያሰገድድ ጥያቄ ለመላክና፣ ከመልሳቸው በኋላ የተሻለ ነው የሚለውን ነገር ለማድረግ ለመወሰን ነው፡፡ የተሠራው ሥራ ባጠቃላይ ይሆናል ብሎ ካሳበው በጣም የተለየ ነው፤ ሰለዚህ በችኮላ ምንም ነገር አያደርግም፡፡ ትናንትና ባሳየው ችሎታ ቴዎድሮሰ ተደናግጠው ከሆነ፣ የቀረበላቸውን ጥያቄ ለማዳመጥ ዝግጁ ነው የሚሆኑት፡፡ "እጅተል እል ሸይጣን"፤ "ችኮላ ሠይጣን ነው!" የአረቦች ጥቅስ ነው፡፡

የእሰረኞቹ ሁኔታና የዘመቻው የመጨረሻ ውጤት በናፒየር ትግሥት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ በፋላ፣ በሰላሴ ወይም በመቅደላ ላይ የተጣደፈ እንቅሰቃሴ ከተደረገ፣ ተሰፋ የቆረጡት ንጉሥ ሙጥኝ ብለው የያዙትን የመጨረሻ የተሰፋ ፍንጣቂ ሊነሳቸው ስለሚችል ያለምንም ጥርጥር እስረኞቹ በፍጥነት እንዲገደሉ ትዛዝ ሊሠጡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም፣ ንጉሡ ራሳቸው ከመቅደላ ምዕራባዊ ሰሜን መቶ ማይሎች ርቀት ወደ ሚገኘው ወደቋራ ሊጓዙ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የዚህ የዘመቻውን አላማና ግብ ለዘላለም ያከሽፈዋል፡፡

እነዚህን መጠነኛ እሰተያየቶች ካየን በኋላ፣ በሰር ሮበርት የተላከውን የእጅ ሰጥ ጥያቄ መልከት የያዘውን ሰው ማንነት እንወቅ፡፡ የሁሉም ጥርጣሬ ወይም ግምቶች ቁልፍ በዚህ መልከተኛ ላይ የተያዘ መሆን አለበት፡፡

መልከተኛው፣ ወደላይ በፋላና በሥላሴ መሀከል በሚገኘው፣ ሸለቆው ወደሚወሰደው መንገድ ግማሽ ላይ ሲደርስ እሱን ባሰገረመው ሁኔታ ሁለት ሰዎች ቁልቁል ሊመጡ ያያል፡፡ ወዲያውኑ እንደታወቀው፣ የወረዱት ሰዎች ሉተናንት ፕሪዶና ሚሲዮናዊው ቄሰ ሚር ፍላድ ነበሩ[124]፤ ከንጉሡ፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር የተላከ መልከት ለማድረሰ በመንገድ ላይ ነበሩ፡፡ ከካምፕ የተላከው መልከተኛም የተላከበትን ጉደይ ሳይፈፅም ከእሰረኞቹ ጋር አብሮ ወደ ካምፕ ተመለሰ፡፡

---

124 ፀሀፊው ባይጠቅሰም፣ ደጃዝማች አለሜ ከነዚህ ሁለት ሰዎች ጋር አብረው ተልከዋል፡፡

እንግዶቹ እንደታዩ፣ ወዲያውኑ ካምፑ ውስጥ ግርግር ተፈጠረ፤ ሰዎች ሰብሰብ ብለው ከነበሩበት ሁኔታ ተበተኑ፤ ወታደሮችም በብዛት፣ በፍጥነት፣ ሥርአት በሌለው ሁኔታ መሰባሰብ ጀመሩ፤ ነገር ግን፣ ወዲያው ደግሞ ይህ ሁሉ ግርግር ወደ ፀጥታ ተዛወረ፡፡ ይህም፣ ቆብ የደፋ፣ አዲስ ቀይ ዩኒፎርም የለበሰና ወርቃማ ማሰሪያ ጠርዝ ያለው መነፅር ያደረገ ሰው በትሩን ይዞ ብቅ ሲል ነበር፡፡

"ይህ ሰው ማነው?" ብሎ አንዱ ጠየቀ፡፡

"ከየትኛው ምድር ነው የመጣው?" ሌላው ደገመ፡፡

"ኢጋድ![125]፣ ይህ ሰው ከሰማይ ነው የወረደው፡፡"

ፕሪዶ በርግጥም አለባበሱ ታላቅ ነበር፤ ዘናጭ ወታደራዊ አለባበስ፡፡

ለትልቁ ጄኔራል አክብሮት ሲል ነበር እንደዚህ የለበሰው፡፡ ስህተት ነበረ ወይ? ሚስተር ራሳም ወደ እንግሊዝ ካምፕ በመሄድ አዛዡን እንዲገናኝ ሲነግረው፣ ያለ የሌለውን የእንግሊዝ መኮንኖች የወታደራዊ የጀግንነት ምልክቶች ደርድሮ፣ ጺሙን በጥንቃቄ ተላጭቶ፣ ከከንፈሩ በላይ ያለውን ሾጠጥ ያለ ጺሙንና ራሱን ከነበረው የሮውላንድ ሽቶ የመጨረሻዋን ጠብታ ተቀብቶ፣ ጫማዎቹ እስኪያብለጨልጩ ድርስ በደንብ ወልውሎ፤ ዩኒፎርሙን እንድ የነጥብ ምልክት እስከማይታይ ድረስ ቦርሾ፤ ሳጥኑ ውስጥ ሳይጠቀምበት የከረመውን የአይን መነፅሩን አፅድቶ፤ ከቦት ጫማው ጋር የሚታሠረውን የፈረሰ መኮልኮያ ሳይቀር ወልውሎ፤ ኮፍያውን ካደረገ በኋላ ማንም የእንግሊዝ መኮንን ሳይዝ የማይወጣውን የእጅ በትሩን ይዞ፣ ጄኔራሉን ለማየት ወረደ፤ ህይወቱስ በዚህ ጄኔራል እጅ አይደለች?

ኮራ ብሎ ሳይጨነቅ የአይን መነፅሩን አስተካክሎ፣ ወጣቱ ፕሪዶ፣ የያዘውን የእጅ በትር እያሽከረከረ ወደ አዛዡ ጄኔራል ድንኳን አመራ፤ ስለ እስረኞቹ መምጣት ሰምቶ የነበረው ጄኔራሉ ራሱ ተቀበለው፡፡

ሉተናንቱ እራሱን ለማስተዋወቅ ጎንበስ ብሎ እጅ ነስቶ ሚስተር ፕሪዶ እንደሚባል ተናገረና ወደ ቴዎድሮስ ከተላኩት የእንግሊዝ ልዑካን አባል መሆኑን ተናግሮ፣ አብሮት የመጣው የእስር ቤት ጓዱ ደግሞ ሚስተር ፍላድ እንደሚባል ተናገረ፡፡ ታስሮ የከረመ ቢሆንም ከሰዎች ጋር የሚደረገውን የግንኙነት ስነሥርአት ህግ አለመርሳቱን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ከጄኔራሉ ፊት ስለሆነም ትንሽ የፍርሀት ምልክት ይታይበታል፡፡ ነገር ግን የጄኔራሉ የታወቀ የመልካም አቀባበል ፀባዩ ለእንደዚህ አይነት ወጣት ሰው ፍቱን ነበረና ምልክቱም ወዲያውኑ ጠፋ፡፡ ወደ ድንኳኑ እንዲገባ ከተጋበዘ

---

125 የመገረም አገላለፅ

በኋላ፣ አስፈላጊም ያልነበረ ግን ስለ እየር ጠባዩ ጥያቄ ከተጠየቀ በኋላ፣ የመጡበት ጉዳይ ተጠየቀ።

ሉተናንቱ እንዲህ በማለት ጀመረ፤ "ከንጉሡ ወደእርስዎ ወደ ሰር ሮበርት ተልኬ ነው፤ የመጣሁትም እነዚህን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ነው። ለምን ወደዚህ ሀገር መጣችሁ? ምንድን ነው የምትፈልጉት? እሰረኞቹ ቢለቀቁ ወደ ሀገራችሁ ትመለሳላችሁ ወይ?"

"እመሰግናለሁ" አለ ሰር ሮበርት በርጋታ፤ "የኔን መልከት ስትመለስ ይዘህ ትሄዳለህ፤ ነገር ግን የትናንትናው ውጊያ ቴዎድሮስ ላይ የፈጠረውን ሁኔታ ንገረኝ።"

ሉተናንት ፕሪዶ ሲናገር፣ ቴዎድሮስ ግዙፎቹን ዝሆኖች ግዙፍ ከሆነ ከጀርባቸው ላይ ከነበረው ጭነት ጋር ከደላንታ በኩል ሲመጡ እንዳዩ፣ ከዚያም በተጨማሪ በሰልፍ የሚመጣውን ነጭ፣ ቀይ፣ የተለያየ ቀለም ያለው ልብስ የለበሱ ሰዎችን፣ እነሱን ተከትሎ የሚመጣውን ማቋረጫ የሌለው የእንስሳቱን መስመር ጨምሮ የወታደራዊውን ትዕይንት ሲያዩ በአድናቆት እንደነበርና፣ በሕይወታቸው የሚመኙት የነበረው ነገር ሊሳካ እንደሆነ እንደተናገሩ ገለፀ። በውጊያ ላይ ወታደሮች፣ እውነተኛ ወታደሮች እንዴት እንደሚዋጉ ማየት እንደሚችሉ ሲያስቡ በኩራት ነበር የተነቃቁት።

ጄኔራሉና አጋሮቹ ከታች ከደልዳላው ሥፍራ ሲታዩ፣ ወዲያውኑ፣ የራሳቸው እለቆችና ወታደሮች ወደታች ወርደው ፈረንጆቹን እንዲወጉ እንዲፈቅዱላቸው እሰጨንቀው ያዟቸው። ትንሽ ካወላወሉ በኋላ፣ የመድፈኞች ቡድን ወደላይ ሲመጣ ተመልከተው፣ በቅሎዎቹ ላይ የተጫነው የጥይት ሳጥን ገንዘብም ያለው ስለመሰላቸው፣ "ሂዱ፣ ልጆቼ፣ ንብረቱን ማርኩና፣ ፈረንጆቹንም እባሯቸው።" አሉ። እራሳቸው ጦሩን ለመምራት አስበው ነበር፣ ግን በታማኝ እዛዦቻቸው ግፊት እንዳይሄዱ ተደረገ።

ከዚያም በቅጥራቸው ስር የነበሩትን ጀርመኖችና መድፍ ሰሪዎችን፣ የመጀመሪያዎችን መድፎች እንዲተኩሱ ትዛዝ ሰጡ። ከትልልቆቹ እንደኛው[126] መድፍ በመጀመሪያው ተኩስ ፈንድቶ ዙሪያውን ከበው የነበሩ ብዙ ወታደሮቻቸውን ገደለባቸው። ያለፈቃዳቸው የሚተኩሱት ጀርመኖች መድፎቹን ሳያነጣጥሩ ሲተኩስ ሲያዩ፣ በጣም ተናደው፣ እራሳቸው መድፎቹን ወደ ኢላማቸው እንዲያነጣጥሩ አደረጉ። ይህ ሁሉ 200 ፓውንድ እሩሮች በተከታታይ እየተተኮሱ፣ ነገር ግን የእንግሊዝ ወታደሮች ያለማቋረጥ ወደላይ ሲመጡ ሲያዩ ጥርሣቸውን እያፋጩ፣ መሬቱን በግራቸው እየደበደቡ በንዴት

126 (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

በእንባ ተዋጡ:: ንዴታቸውን የጨመረው ደግሞ ምርጥ ወታደሮቻቸው በእንግሊዞቹ መድፎች ሲወድቁ ሲያዩ ነው::

ቀጥለውም፣ ለዚህ ውድቀት እስረኞቹ ዋጋቸውን መክፈል አለባቸው ብለው ዛቱ:: ምሽቱ ሲመጣና ጦርነቱ ሲቆም መሪር ስሜታቸውንና መንፈሳቸውን ጋብ ለማድረግ አረቄ መጠጣት ጀመሩ::

ሕሊናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት እዲሰና ከመጠን በላይ በመሆኑ፣ መርሳት የሚችሉበት ደረጃም አልነበረም:: ሶስት ጊዜ ራሳቸውን ለማጥፋት ሞክረው በረዳቶቻቸው ብርታት በጥበቃ ሊያስጥሏቸው ችለዋል:: በጥልቅ ጭንቀትም የምርጥ ጀኔራሎቻቸውን ስም ይጠራሉ፤ ፊታውራሪ ገብርዬ[127]፣ ደጃች ደረሰ፤ ደጃች ወርቄ፤ ረዳቶቻቸው ምንም ቃልም መተንፈስ አልቻሉም፤ ዝም ብለው ብቻ፣ አንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ገናና የነበሩት ንጉሥ ያሉበትን የሚያሳዝን ሁኔታ በመመልከት ተወሰነዋል::

ከዛም፣ በመበሳጨት ጀግና የወንድ ወታደሮች ነበሩኝ፣ አሁን የቀሩት ሴቶች ብቻ ናቸው ይላሉ:: የአልቂቱን ውጊያ ባሰቡ ቁጥር ሰውነታቸውን ያንቀጠቅጣቸዋል:: ናፒየር እስኪገርመው ድረስ ፍላድና ፕሩዶ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የሆነውን ደጋግመው ነገሩት::

እፍታም ዝም ብለው፣ እይናቸውን አፍጥጠው፣ የሚያስቅቀውን ባሏቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች የሚያሰሙትን ለቅሶ ይሰማሉ::

በቁጣ፣ "የእነዚህን ሴቶች ለቅሶ አስቁሙልኝ" ይላሉ::[128]

የደረሰው ሽንፈት፣ ድንገተኛ፣ ከባድና ሰፊ በመሆኑ ጥልቀቱን በልክ ገና ማመዛዘን አልቻሉም::

"ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጡብንን ፈረንጆችን ሄዳና ግደሉ::" ብለው ወታደሮቻቸው ላይ ጮሁባቸው::

"የለም፣" ሽበቶ እማካሪያቸው ነበር፣ "ያቆዩዋቸው፣ ሁለቱን ወደ እንግሊዙ ጄኔራል ይላኩና የሚለውን ይሰሙ"[129]

"እሃ፣ እዎ፣" አሉ በሃሳብ ተውጠው:: "ያ ይሻላል:: ሱልጣን ራሳምን ወደኔ አምጡልኝ" አሉ::

ይህ የሆነው አሮጌ ላይ በደረሰው እልቂት ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ነበር:: የስቅለት ቀን ነበር:: ራሳም፣ ከዚህ በፊት እንደገለጥኩት፣ የንጉሡን ስሜት ማለስለስ የሚችል ሰው ነበር::

---

[127] ፊታውራሪ ገብርዬ (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

[128] (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

[129] (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

ራሳም ከቦታው ደረሰና፣ ለንጉሡ በሚገባ መንገድ እጅ ነሳ። ሰላምታው ራሱን ዝቅ ባደረገ ስሜት ነው የቀረበው። በንፁህ ልብ በተሞላ ተሰፋ ያቀረበው ንግግር፣ "ገናናው ንጉሥ፣" "የአለም ገዥ፣" "የህዝቡ ታዳጊ"፣ "ሀያሉ ጌታ፣ የክርስትና ሀይማኖት ጠባቂ" አድሜዎን ያርዝመው።

ከዚህ ቀደም የተሰማቸውን ስሜት እንደምንም አፍነው፣ ንጉሳዊነት በተሞላበት ግርማ ሞገስ ከተቀመጡበት በመነሳት፣ በራሳቸው ሀር የተሸፈነ መቀመጫ ላይ እንዲቀመጥ ጋበዙት። አጠገቡም፣ ጠጅ፣ ጠላና አረቄ ነበር። በተዝናና ሁኔታና በትህትና፣ ለንጉሡ ጤንነት፣ ራሳም የቀረበለትን መጠጥ ጠጣ።

ራሳምን የላከው ሀገር ሰዎች በጀግንነት ለመዋጋታቸው አመስግነው፣ ቴዎድሮስ፣ ራሳምን፣ "ምን ላድርግ?" ብለው ጠየቁት።

ራሳም የተለያዩ ሀሳቦችን ቢደረድርም፣ ንጉሱ፣ አንዳቸውንም ለማድረግ አእምሯቸው አልፈቀደም። ነገር ግን፣ ከአሰረኞች ሁለቱን ልኮ፣ የፈረንጆቹ አዛዥ ምን እንዳቀደ ማረጋገጥ ይሻላል ብለው አሰቡ።

ራሳም በሀሳቡ ተሰማምቶ፣ ሚስተር ፍላድና ሉተናንት ፕሩዶ የሚታመኑ ስለሆኑ እነሱ ቢላኩ የሚሻል ነው ብሎ ሃሳብ አቀረበ።

"መልካም!" አሉ ቴዎድሮስ፣ በከፍተኛ ሀኔታ ተረጋግተው፣ "የኔን ምስጋናና መልከት ለጄኔራሉ እንዲያደርሱ እንዲዘጋጁ ንገራቸው።" አሉ።

ከዚያም በወንድማማችነት ተቃቀፍው፣ ከመለያየታቸው በፊት ብዙ የመልካም ስሜት መግለጫ ቃላት ተለዋወጡ።

ይህን ሁሉ የሰማሁት ከሌሎቹ አሰረኞች ነበር።

ሉተናንት ፕሩዶና ሚስተር ፍላድ ከጄኔራሉ ጋር ምሳ በሉ። በዚህ ጊዜም ከላይ የተነገረው ሁኔታ ለጄኔራሉና ለጥቂት ረዳቶቹ ተደጋግሞ ተነገረ። የቀረበው ምግብ፣ እነዚህ ሁለቱ አሰረኞች እንዳደረጉት አይነት እንዲዚህ ሆኖ ተጣጥሞ ተበልቶ አያውቅም።

ሉተናንት ፕሩዶ ከጠሩ መኮንኖች ጋር ከተነጋገረ በኋላ፣ ሁለቱም መልከተኞች ለቴዎድሮስ ስለሚወስዱት መልከት መመሪያ ተሰጣቸው። "በኔ ሰም!" እንዲህ ብላችሁ ንገሩ አለ ሰር ሮበርት። "የምጠይቀው፣ አሰረኞቹ ከነንብረታቸው በአሰቸኳይ እንዲፈቱ፣ ራሳቸው እጅ እንዲሰጡና፣ የሰላሴ፣ የፋላና የመቅደላ ምሽጎችን ከውስጡ ካለው ንብረት ጋር እንዲያሰረክቡ፣ ይህንን ካደረጉ የሚገባቸውን ክብር እንድምንሰጣቸው ላረጋግጥላቸው እንደምችል ነው።"

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ሁለቱ አሰረኞች ከቴዎድሮስ ጋር ከቆዩ በኋላ ተመልሰው መጡ። ቴዎድሮስ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ከናፒየር በተላከው

መልከት ምክንያት በቁጣ ገንፍለው ነበር። በመልከታቸውም፣ ንጉሥ እንደመሆናቸው መጠን፣ የእንግሊዙ ጄኔራል፣ ሌላ የተሻለ መደራደሪያ እንደሚሰጣቸው ፀሎታቸው እንደሆነ ገልፀው፣ ለሴት[130] ለሚያገለግል፣ ለማንም አለቃ እጃቸውን እንደማይሰጡ አስታወቁ። "አለዚያ" አሉ ቴዎድሮስ በላኩት መልከት፣ "እጄን ከምስጥ እስከ ሞቴ ድረስ አዋጋለሁ። የመጣችሁበት ምክንያት የሆኑት ሰዎች ካገኛችሁ አይበቃችሁም ወይ፣ ለምን እኔን በሰላም አተዉኝም?"

ሰዎቹም፣ ወደ አስራ አንድ ሰአት አካባቢ፣ የመጀመሪያውን አይነት መልስ ያለበትን መልከት እንዲያደርሱ ተላኩ። "ለእንግሊዝ ንግሥት ያሰምንም ቅድሚያ ሁኔታ እጅዎን እንዲሠጡ፣ የሚገባዎትን ክብር እንደምንሰጥዎ አይጠራጠሩ።" የሚል ነበር።

መላው የእንግሊዝ ሠራዊት እነዚህን መልከተኞች በጣም በሃዘኔታና በርህራሄ መንፈስ ነው ያያቸው። ቴዎድሮስ፣ በቁጣና በቂም በቀል በእናታቸው ላይ ሊያወርዱባቸው የሚችሉትን አስፈሪ ጥፋት አስቀድሞ በማሰብም ነበር።

ፍላድና ፕሩዶ ሁለተኛውን የተሻለ የድርድር ጥያቄ ይዘው ወደ እንግሊዞች ካምፕ ሲመለሱ፣ የራሳም፣ የአዋቂነት መንፈስ፣ ዙሪያውን ከነበረው አጠራጣሪ የጭጋግ ሽፋን ዘልቆ መታየት ጀመረ።

"ጃንሆይ! ይመኑኝ። ሁሉንም እስረኞች ወደ እንግሊዝ ካምፕ ይላኩ። እኔ ራሴ፣ የእንግሊዙ ጄኔራል ወደ እገሩ እንዲመለስ ዋስትና እለጣለሁ።"

እንደኔ ግል አመለካከት፣ ራሳም በተናገረው ነገር ከልቡ አምኖበት ነው። ምክንያቱም፣ ከሚገባው በላይ፣ ለዘመቻው እሱ ብቻ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ አድርጎ ነው ያሰበው። የሌሎቹ እስረኞች መፈታትና፣ ቴዎድሮስን የመቅጣቱ ሁኔታ በሁለተኛ ደረጃ እንደሆነ አድርጎ ነው የገመተው። እንግዲህ፣ ንጉሡ ነገሰቱም ቢሆን፣ በራሳም በመተማመን፣ ከከሩሲደሩ አዛዥ ጀኔራል ጋር ሊያስማማቸው የሚችል ተፅዕኖና ግፊት ማድረግ እንደሚችል አምነው ተቀበሉ[131]። ከዛም፣ ሁሉንም እስረኞች ወዲያውኑ እንዲሰበስቡ፣ ያላቸውን ማንኛውንም ንብረት ይዘው በምሽጉ ዋና በር በኩል፣ ወደ ቃፊር በር እንዲሄዱ እንዲያደርግ ትዛዝ ሰጡት። ሁሉም ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ሰዎቹን ለመሰናበት ወደ በሩ እንደሚመጡ ነገሩት።

---

130 ንግሥት ቪክቶርያን በመጥቀስ

131 ሌሎች ፀሀፊዎችም በዚህ ጉዳይ፣ ንጉሡ ራሳምን ወሳኝ ሰው አድርገው እንደተመለከቱት ነው የሚገልፁት። የሚነሳው ጥያቄ፣ ራሳም በብልጠቱ ንጉሡን አታሏል ወይ? ነው።

በማይታመን ፍጥነት፣ እስረኞቹ ባንድ ላይ ተሰብስበው፣ የራሳቸውን አገልጋዮች፣ የአገልጋዮቻቸውን አገልጋዮችና ባሮቻቸውን ይዘው ቃፊር በር ላይ ተሰበሰቡ፡፡

ይህ የተሰያዩ ሰዎች ሰብሰብ እንግዳ የሆነ ግርግር ሁኔታ ነበረው፡፡ የነጭና የጥቁር ፊት አንድ ላይ ተደባልቋል፡፡ በፍጥነት ለመውጣት በነበራቸው ጉጉት፣ እንደ ባቢሎን ግንብ ሥራ፣ በዚህ ግርግር መሀል የተለያየ ቋንቋ ሲነገር ይሰማል፡፡ ምንም አይነት ሥርአትም አልነበረም፡፡ በራሳም የተነገራቸው፣ መቅደላን፣ ከደም መፍሰስ ጋር ከተያያዘው ከነአሰቃቂ ትዝታው ለዘላለም ለቀው ለመሄድ በግማሽ ሰአት ውስጥ እንዲዘጋጁ ነበር፡፡ ወዲያውኑ፣ ሁሉም የትም ይሁን ብቻ ወደየቤታቸው መሄዳቸው ነው የታያቸው፡፡

ብዙም ሳይጠብቁ፣ ቴዎድሮስ፣ የሚኮሩበትን እልባሳት ለበሰው ከዋና ዋና ሰዎቻቸው ጋር በመሆን ወደ በሩ መጡ፡፡ ከአንድ ሰው በለተቀር ሁሉም እሰረኞች እጅ ነሱ፡፡ ንጉሡም፣ በሩ እንዲከፈት ትዛዝ ሰጡና፣ እስረኞቹ በፊታቸው ሲያልፉ እጅ እየነሱ በበሩ ወጥተው መሄደ ጀመሩ፡፡

“ካሜሮን፣ ደህና ሁን፡፡" ቴዎድሮስ ቆንሰላውን ነበር ያናገሩት፡፡ "ወዳጆች እንደሆን ነው የተለያየነው፣ ተሰፋ አደርጋለሁ?" አሉ፡፡

ለተሰጠው የሰንበት ሰላምታ፣ መልሱን በትህትናና በአከብሮት መመለሱ በቆንሰላው እንደበት ላይ ነው ያለው፡፡ በንጉሡ ላይ የሚመጣውን ውድቀት በማወቁ፣ ለገዥው የፀፀት ሀዘኔታ እንዲሰማው አድርጎታል፡፡ ነገር ግን ቃላቶቹ በሰርአት ወይም ለስለሰ ባሰ እንደበት መውጣት አልቻሉም፡፡ እንደ ምናብ ፅጌረዳም፣ በከንቱ ያሳለፈው የህይወት ጊዜው ፊት ለፊቱ ታየው፡፡ ከዚህ በፊት የነበረበትን ሁኔታም ሲያስታውሰ፣ ግራጫ መልከ ባለው በቆሸሸ ብርድ ልብሰ ተጠቅሎ ከእሰር ቤት ግድግዳ ጋር መታሰሩ ነበር፤ ጭካኔ የተሞላበት ሰቆቃ፣ ሰንበር የሚያወጡት እለንጋዎች፣ ለረዥም ጊዜ በሱ ላይ ሊደርስ የሚችለው ዕጣ ፈንታው፣ እህ፣ ያሳለፉቸው የረዥም ቀናቶች የእእምሮ ሰቃይና ፍፁም እንግልት፣ ቀኖቹ ተራ በተራ ሲያልፉ የሚታወሱት፣ ማቋረጫ የለሌው ቅጣት፣ በግልፅም፣ ወላዋይ በሆነና ባልተዘጋጀው በራስ መንግሥት ጥረት አለመደረጉ ሁሉ ነበሩ፡፡ እናም ለዚህ ሳከሰናዊ ሰው ምን እይነት መንፈሰ ቢኖረው ነው ይህንን እምባገነን ሰው ይቅር የሚለውሰ፡፡ ነገር ግን የነበረበት ሁኔታ በጣም አደገኛ ሰለሆነ፣ የነበረው ፖሊሲ፣ የቴዎድሮሰን ሰንበት እንዲቀበል አድርጎታል፡፡

“ደህና ይሁኑ ጃንሆይ፡፡" በማለት በክብር ሰላምታውን በመመሰስ ቆንሰላው ካሜሮን እልፎ ሄደ፡፡

"ደህን ሁን፣ አቶ ኮከቤ(ስተርን)፡፡ ለበደልኩህ ሁሉ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡"

የከርሰትና እምነቱ ይቅርታ እንዲያደርግ ገፋፍቶት ይሆን፣ ወይም ደግሞ ቴዎድሮስን ፍራቻ ይሆን፣ ሳይታወቅ፣ እውነታው ግን፣ ሚስተር ስተርን፣ እጅ በመንሳት "ደህና ይሁኑ ጃንሆይ፡፡" አለ፡፡

"አሃ፣ ከረንስ፣ አንተ ነህ? ደህና ሁን፤ ከዚህ በኋላ አላይህም፡፡"

ወጣቱ ከረንስ፣ በወጣት ስሜቱ፣ የተበደለው ሁሉ ስሜት ገና በአእምሮው ትኩስ አያለ፣ ወደ ቴዎድሮስ ሄዶ እጃቸውን ይዞ፣ ራሱን ደፍቶ እጅ ነስቶ፣ "ደህና ይሁኑ ጃንሆይ፣ መልካሙን እመኝልዎታለሁ፡፡" አለ፡፡

"አሃ፣ ሱልጣን ራሳም ደህና ሁን፡፡ ከእንግሊዙ አለቃ እንድታስታርቀኝ በአንተ እተማመናለሁ፡፡ ነገ ጥሩ ወሬ ይዘህ ወደኔ እንደምትመጣ እርግጠኛ ሁን፡፡"

"በርግጥ፣ ጃንሆይ፡፡ ነገ ጥሩ ወሬ ይዤ እንደምመለስ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ሰላም ይደሩ፣ የኔ ንጉሥ!" ይህን ብሎ፣ በመግቢያው በር መከላከያ አጥሩን አልፎ የታችኛውን ማማ አልፎ ሄደ፡፡ እራሱና ሌሎቹም፣ ነፃና ጤናማ አየር ተነፈሱ፡፡ ከመቅደላ፣ በሰላምጌ በኩል፣ ሰላሴን ዞሮ፣ ፋላን ተጠግቶ በመውረድ፤ ከዛም ረዘም ያለ ወጣ ገባ ወርደው የእንግሊዞች ካምፕን አልም ብልጭ የሚሉ መብራቶች ሲያዩ የጋለ ተሰፋ በውስጣቸው ተነሳሳ፤ ግልፅ ባለው የማታ አየር፣ ሁሉም በአንድነት ከጭንቀት በተረፈው ልባቸው ምስጋና አቀረቡ፡፡

ዜናው በጦሩ መሀል ወዲያው በመሠራጨቱ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች እሰረኞቹን ለመቀበል ወደ ዋናው አዛዥ ጽ/ቤት እየተጣደፉ ሄዱ፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰአት ሲሆን፣ እየወረደ የሚመጣው የሰዎች ሰልፍ የመጀመሪያው ክፍል ካምፕ ውስጥ ደርሶ፣ የጠቅላይ አዛዡ ድንኳን ፊትለፊት ቆመ፡፡

ሳንጃ የያዙ ጠባቂ ወታደሮች ተመልካቾቹን በመግፋት፣ ለመንገደኞቹ ከፍተት ቦታ ፈጠሩ፡፡ ሰዎቹ እንደደረሱም፣ ደከም ያለ የደስታ ሰሜት ድምፅ (ቺርስ) እንደመጀመር አለና ወዲያውኑ ግልፅ ባልሆነ ጉርምርምታ ተተካ፡፡ ቺርሱን የጀመረው ሰውም የሚከተለው ሰው እሰመኖሩን ሲያውቅ አቆመ፡፡

ሴቶችና ልጆች ነበሩበት፣ የህፃን ልጅ ቀጭን ድምፅ ሲሰማ፣ የተሟሟቀ ቺርስ እንደማሰማት ፈርጠም ያሉት ወታደሮች መሳቅ ጀመሩ፡፡ በርግጥ ይሰቁ ጀመር፡፡

በርግጥ፣ አንድ የማይሆን ነገር መኖር አለበት፡፡ ይህ፣ እስረኞቹ ከመለቀቃቸው በፊት የጠበቁት አቀባበል አልነበረም፤ ተሰፋ ያደረጉበት መልካም ሁኔታም አልመሰለም፡፡

እልነበረም፣ እኔ ያየሁትን ልናዘዝ፡፡ እኔም የገመትኩት፣ ሁሉም የሠራዊቱ አባላት እንደ አንድ ሰው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሁራ በማለትና በብራሰና አንድ ላይ በማጋጨት ድምፅ በሚሰጡት ሲምባሎች ጩሀት የሚታጀቡ፤ ሁሉም በደሰታ የሚቅነዘነዙ፤ እስረኞቹም ቢሆን በደሰታ የሚያለቅሱ፤ በምሲጋና ሮጠው የሰር ሮበርት ጉልበት ስር ወድቀው እግሮቹን አቅፈው እጆቹን የሚስሙ፤ ሰር ሮበርትም አጋጣሚውን በመጠቀም ሰለ መልካም አመራርና ውጤቱ ንግግር የሚያደርግና፤ ከዛም እጆቹን ወደላይ አድርጎ ፊቱን ቀና አድርጎ ነፃ ለወጡትና ለነፃ አውጭዎቹ የእግዚአብሔርን በረከት የሚጠይቅ ነበር፡፡ እንግሊዛውያን ይህን አይነት ነገር ከዚህ በፊት አድርገዋል፤ ነገር ግን፣ እንግዳ በሆነ ሁኔታ እዚህ ቦታ ግን አላደረጉትም፡፡

መኮንኖቹ የአይን መነፀራቸውን ማድረግ ሲጀምሩ፤ ላንዳፍታ እንኳን ሁኔታውን ለተመለከተ ሰው፣ ዘጠና ዘጠኝ የሚያንፀባርቁ መስታውቶች፣ በዘጠና ዘጠኝ ሰዎች አይን ላይ ተሰክተው፣ ዘጠና ዘጠኝ የሚሆኑ አዋቂ ሰዎች፣ ኮለተር ብለው እሰረኞቹን ሲመለከቱ በማየት ምስክርነተ ይሰጥ ነበር፡፡ መኮንኖቹ የእሰረኞቹን ሁኔታ አጥብቀው በማየት፣ የለበሱትን ልብሰ ቁልፍ፣ ረጋ ብለው ስለሚታዩት ህፃናቶቹና ሰለ ሴቶች አሰተያየት ይሰጣሉ፤ በመጨረሻም ያለምንም መገረም የሴቶችን ዕድሜም እሰተዋሉ፡፡

ባጠቃላይ፣ ምርኮኞቹ፣ ለኛ ከተነገረንና ከጠበቅነው በላይ በጣም የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከሶሰት ሰዎች በሰተቀር፣ ሌሎቹ በሙሉ ደህና ይመስላሉ፡፡ ወጣቱ ከረንስ፣ የካሜሮን አገልጋይ የሆነው የአየርላንደ ተወላጁ መከኤልቪና የቴዎድሮስ መሀንዲሰ የነበረው መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሽራይበር ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች ገርጠት ብለው፣ እንደ ሮማውያን ረዘም ያለ አጀ ጠባብ የመሰለ ለብሰው፣ ራሳቸው የሰሩትን የሰሴን ባርኔጣ አድርገዋል፡፡ የአየርላንዱ ልጅ፣ ማከኤልቪ፣ ከሚገባው በላይ ደሰተኛና ፍንድቅ ያለ ነበር፡፡

መቅደላን ለመልቀቅ በነበረው ችኮላ፣ ወይዘሮ ፍላድ በራሳም ተረሰታ ወደኋላ ቀርታለች፤ በመጠኑም ቢሆን ህመምተኛ ነበረች፡፡

ሚሰተር ፍላድ፣ ድፍን ባለው ሌሊት ልጆቹና ባለቤቱን ለማምጣት ወደ መቅደላ መመለሰ ነበረበት፡፡ ፍላድና ፕሩዶ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ መቅደላ ሲመለሱም፣ እሰረኞቹ፣ በፋላ ቁልቁለቱን ይዘው ሲመጡ ተላልፈዋል፡፡

እሰረኞቹ እንግዲህ እነዚህ ናቸው፤ ጠቅላላ ቁጥራቸው ስልሳ አንድ ነበሩ፡፡ ለነዚህ ነው እንግዲህ ዘመቻው የተካሄደው፡፡ እነዚህ ነበሩ እንግዲህ

ሲልኩ በነበሩት አሳዛኝ ደብዳቤ የእንግሊዝ ክርስቲያኖችን እንባ ሲያስፈስሱ የነበሩት፡፡ እንደ ደብዳቤያቸው አገላለፀ፣ ሁላችንም ሊሞቱ የተቃረቡ ናቸው ብለን እንድናምን አድርገውናል፡፡ ይህም፣ በየቀኑ ይገረፉ እንደነበር፣ ሁልጊዜ በእግር ብረት እንደታሰሩ፣ ርቃናቸውን፣ አካላታቸው ላይ ብዛት ያለው ቁስልና ጠባሳ ያለበት እንደሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ሲታዩ፣ በደንብ የለበሱ፣ በተለይ እራቱማ የአይን መነፀር ያደረጉ ነበሩ፡፡ አስገራሚ!

በእሳት የተግለበለበው፣ ለብዙ አቢሲኒያውያን ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነበት የሰቅለት ቀን አልፎ የሚቀጥለው ቀን ነጋ፡፡

ከታመሙት ወይዘሮ ፍላድና ባርዴል በስተቀር፣ ሁሉም እስረኞች በኛ ካምፕ ውስጥ ነበሩ፡፡ የነሱ፣ ጥቁር፣ ነጭና ቀይ ድንኳኖቻቻው ከሠራዊቱ ድንኳኖች በቁጥር ይበልጡ ነበር፡፡ እንደ ዝርዝሩ ከሆነ፣ ሰልሳ አንድ ሰዎች መኖር ነበረባቸው፤ በቦታው አርባ ሰምንት ድንኳኖች ነበሩ፡፡

ከነዚህ እሰረኞች ጋራ፣ 187 አገልጋዮችና 323 እንስሶች ነበሩ፡፡ ወይዘሮ ፍላድ ከጠዋቱ 3 ሰአት ሲሆን በሰላም ደረሰች፡፡ በመቅደላ የቀረ አንድ ብቸኛ ሰው፣ እርቲሰቱና ፐሮፌሰሩ ባርደል ነበር፤ እሱም ትኩሳት ያለበት በሽታ ይዞት ነበር፡፡ መታወሰ ያለበት፣ ይህ ሰው ነበር እንግዲህ የሚሲዮናውያኑን ደብዳቤ ለቴዎድሮስ በማስተርጎም፣ ንጉሡን የሚሰድብ ፅሁፍ ፅፋችኋል ተብለው እንዲገረፉ እስደረገ ተብሎ የሚወቀለው፡፡ ሰልሳ አንድ ሰዎች ናቸው ብዬ ነበር፡፡ ሰልሳ ሁለተኛዋ ደግሞ፣ እንግሊዝ ካምፕ ከደረሱ በኋላ በነጋታው ከጠዋቱ እራት ሰአት ላይ የተወለደችው ቴዎዶራ ሞሪተዝ ነበረች፡፡ ሰሟም የወጣላት በንጉሡ በቴዎድሮስ ሰም ነው[132]፡፡

የፖለቲካ ፀሐፊው ቲዊዲ፣ የእስረኞቹንና የተከታዮቻቸውን ሰም ዝርዝር ሲያነብ ከሚገባው በላይ ነበር የተደነቀው፤ በተለይም ከሰራተኞቹ እንድ ሶስተኛ የሚሆኑት የአቢሲኒያ ሴቶች መሆናቸውን ሲያውቅ የበለጠ ነበር የተገረመው፡፡

ይህን ዝርዝር ውነታ በሰሙ ሰዎች በሙሉ የሚያንገሸግሽ ጥላቻ ሰሜት ነው የተፈጠረው፡፡ ከእሰረኞቹ የተፃፉት እሳዛኝ ደብደቤዎች መታመን የማይችሉ ለመሆናቸው መረጃ የሚሆኑ ሌሎች አሰገራሚ ውነታዎች መውጣት ጀመሩ፡፡

---

[132] ልጃቸውን የንጉሡን ሥም ሲሰጡ፣ ንጉሡን ያን ያህል ይጠሉ ነበር ወይ?



የተለቀቁተ እስረኞች ከቤተሰብና ሠራተኞቻቸው ጋር
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

አንግዲህ፣ ሥጋ፣ ዳቦ፣ ማር፣ ወተት፣ ቤት፣ አትክልት፣ ወይን ወዘተ ካላቸው፣ ሌላ ምን ተጨማሪ ፈለገው ነው ብለን ተገረምን::[133]

መቅደላን ከተቆጣጠርን ጀምሮ በሁለት ማይሎች ርቀት ውስጥ ምንም አይነት ውሀ ሊገኝ አልተቻለም:: በሁለተኛው ቀን የሚመጣልን ውሃ ሳይደርስ ቀረ፤ የማመላሻው መንገድ በሚሰርቁ ኦሮሞዎች ስለተጥለቀለቀ፣ በቅሎዎቻችን በተደጋጋሚ በነዚህ አጭበርባሪ ሰዎች ይወሰዱብን ነበር:: የሚቀርበው ውሃ ለነበሩን እንስሳት በሙሉ፣ አስር ሺ፣ ለሚሆኑት በቂ አለመሆኑ ሲታወቅ፣ ሁሉም እንስሳት ሰባት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ በሽሎ ወንዝ እንዲወርዱ ተደረገ:: 500 የሚሆኑት ለሠራዊቱ ከወንዙ ውሃ እንዲያመላልሱ ተመደቡ::

የሚያዝናኑ ነገሮች እንደ አልኮል፣ ሲጃራ፣ ትምባሆ፣ ስኳር፣ ሻይ፣ ቡና፣ ሩዝ የመሳሰሉት አንዱም እንኳን የለንም፤ ምክንያቱም ሁሉንም ከነበረንበት ካምፕ አጠገብ ጥለን ነው የመጣነው::

አኩለ ቀን ላይ፣ የፋሲካን በአል ምክንያት በማድረግ፣ ቴዎድሮስ፣ አንድ ሺ ሰንጋ ከ500 በጎች ጋር ለናፒየር ሲልኩ፣ የብሪታንያ ወታደሮቹ አስኪጠግቡ ድረስ መብላት ነበረባቸው፤ እኛስ ብንሆን ክርስቲያን አልነበርንም?

ሰር ሮበርት ግን፣ የዚህን መልክት መምጣት ወዲያውኑ እንደሰማ፣ አንድ መኮንን ወደመቅደላ ልኮ፣ ንጉሡ ራሳቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና የመቅደላ ምሽግን ለእንግሊዝ ንግስት አስካላስረከቡ ድረስ ከንጉሡ ምንም አይነት ሥጦታ ለመቀበል የሚያስበው ነገር አለመሆኑን ይገልፃል:: [134]

ከቀትር በኋላ ከነበሩት አጣናዎች ብዙ የግምብ መውጫ መሰላሎች መሰራት ተጀመረ:: የባሩድ ዱቄቶች፣ ለአጅ ቦምቦች አገልግሎት እንዲውሉ ተዘጋጁ::

አርባ ሁለት የሚሆኑት ዝሆኖች አርምስትሮንግ የተባሉትን ከባድ መሳሪያዎች ወደ ካምፕ ካመጡ በኋላ፣ ማምሻውኑ መሳሪያዎችን፣ በፋላና የኛን ካምፕ የሚለያየው ጉብታ ላይ አደረሱ:: በቅሎዎችም ቢሆን፣ ከሁለት

---

[133] ይህ ሁኔታ ሊተኮርበት የሚገባ ነገር ነው:: ቀደም ባሉ ክፍሎች፣ እስረኞቹ በየቀኑ እንደሚደበደቡ እንደሚሰቃዩ ነበር የሚፅፉት። የነሱ ፅሁፍም ነው፡ በውጭው አለም ለንጉሡ ስም መከፋት ዋነኛ ምክንያት የነበረው:: ሲፈቱ ግን፣ ታዛቢዎች እንዳዩት ሀሰተኞች ነበሩ:: በዚህ ዘገባ የአሜሪካው ጋዜጠኛ ፅሁፍ በመጠኑም ቢሆን ከወገንተኛነት ራቅ ያለ ያደርገዋል::

[134] አፄ ቴዎድሮስ ለጄኔራል ናፒየር የላኩት (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

ቀን መኖ ጋር ከታች ከበሽሎ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ በነጋታው ሊደረግ በታቀደው የመቅደላ ጥቃት ዝግጁ እንዲሆኑም ነው፡፡ ጥቃቱ የታሰበው እኩለ ቀን ላይ ነው፡፡

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ከመተኛቱ በፊት፣ ችግሩን በወዳጅነት ለመፍታት በጣም አነስተኛ ዕድል ባለበት ሁኔታ፣ የከፋ ሰው ላለመሆን ሲል፣ በተወላጆች በኩል እንደገና የመጨረሻ የእጅ ስጥ መልክት አስተላለፈ፡፡ በደብዳቤው ሲገልጽ፣ መከራከሩ አጉልና ውጤት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ፣ ቴዎድሮስ እጃቸውን ቢሰጡ በክበሬታ ሊያዙ እንደሚችሉ ቃል ገብቷል፡፡ በእዋጁ መሰረትም፣ ቴዎድሮስ በነጋታው ጥዋት ሶስት ሰአት ድረስ የፈቃደኝነት መልስ ካልመለሱ መቅደላን ለማጥቃት እንደሚንቀሳቀስ ይገልጣል፡፡

## የምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች

***ቁጥር 126፤*** *የፈነዳው መድፍ ቴዎድሮስ የሚባለው ነበር:: ትልቁ ግን ሴባስቶፖል ነበር:: የሰየሙት ቴዎድሮስ ናቸው:: በዚህም፣ በክሬሚያ ጦርነት የነበራቸውን አትኩሮት ያመለክታል:: ሩሲያዎች፣ ክሬሚያን ለመከላከል፣ በዋናው ከተማ፣ በሴባስቶፖል መሽገው ተቀምጠው ነበር:: እንግሊዞች፣ ቱርኮችና ፈረንሳዮቹ ተባብረው ሩሲያኖቹን መውጋታቸው፣ ከራሳቸው ሁኔታ ጋር የመመሳሰል ባህሪ ሊኖረው ይችላል:: በተጨማሪም፣ የጦርነቱ ዋና ምክንያት፣ በቱርክ ግዛት ስር ለነበሩ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት፣ ሩሲያውያን ሀላፊነቱ የኛ መሆን አለበት ስላሉም ነው:: ለአፄ ቴዎድሮስ፣ ቱርኮች፣ የቆዩ ጠላቶቻቸው ሊሆኑ፣ እንግሊዞቹ ደግሞ አዲሶቹ ናቸው:: ፈረንሳዮቹም ቢሆን፣ ደጃች ንጉሴን(አገው ንጉሤ) አያባበሉ፣ ቴዎድሮስ ላይ እንዲሸፍት አድርገው ነበር:: እንደተጠቀሰው፣ እሳቸው ፊት የሚጎናተሉት ፈረንሳዮችና እንግሊዞች፣ ግንባር መፍጠራቸው አስገርሟቸዋል::*

***ቁጥር 127፤*** *ፊታውራሪ ገብርዬ የቀዳሚው ጦር አዛዥ ነበር፤ በአሮጌው ጦርነት፣ ሙሉ የክብር ልብሱን ለብሶ ሲዋጋ ስለነበር ንጉሡ ይሆናል በሚል ግምት ብዙ ጥይት ነው ያረፈበት:: የሱን አስከሬን ለማንሳት የሞከሩ ሌሎች አለቆችም አጠገቡ ወድቀዋል:: የገብርዬ አስከሬን ሊላክ፣ ቴዎድሮስ ናፒየርን በጣም ነው ያመሰገኑት:: ሆኖም፣ አስከሬኑ የተላከው በደግነት ሳይሆን ተስፋ ለማስቆረጥ የነበረ ይመስላል:: ገብርዬን መጀመሪያ በጥይት የመታው ካፒቴን ስፒዲ ነው ይባላል:: የኋላ ኋላ፣ ስፒዲ፣ የገብርዬን ለምድ፣ ጋሻና ጦር የግሉ አድርጓል፤ በምስሎች ላይ ለብሶ የሚታየውም የገብርዬን የጦር ልብስ እንደለበሰ ነው::*

***ቁጥር 128፤*** *አፄ ቴዎድሮስ ገና ሥልጣን እንደያዙ ያገዱት ነገር፣ በካምፓቸው ውስጥ በጩኸት ማልቀስን ነው:: ስለዚህ ያሁኑ ቁጣ አዲስ አይደለም:: ከዚህ በተጨማሪ ሰው ሊሞት፣ በሀዘን ስም ሰውነትን መጉዳትና ፀጉር መላጨት የአረመኔ ባህል ነው ብለው ስለሚያምኑ በአዋጅ ከልክለው ነበር:: በመቅደላ፣ የአቶ ሳሙኤል ሚስት አባቷ ሊሞቱ ፀጉሬን እላጫለሁ ብላ ባልየው ከልከሏት ነበር::*

***ቁጥር 129፤*** *እዚህ ላይ ሌሎች መረጃዎች የሚሉት፣ ቴዎድሮስ አለቆቻቸውን ሰብስበው እነዚህን እስረኞች ምን እናድርጋቸው ሲሉ፣ አለቆቹ እንግደላቸው ሲሉ፣ እሳቸው በቁጣ፣ ያውም ሃሳብ ያቀረበውን ሰው ሰደበው፣ እስረኞቹ እንዳይገደሉ ተወስኗል:: ይህንን የሰማው፣ ቫልድማየር ነበር:: ይህ እንግዲህ ከዚህ ቀን በፊት የተደረገ ሊሆን ይችላል:: የውጭ ፀሐፊዎች ሰዎቹን፣ ምርኮኞች ይሏቸዋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እስረኞች ናቸው::*

***ቁጥር 134፤*** *አፄ ቴዎድሮስ ለጀኔራል ናፒየር የላኩት የመጨረሻ ደብዳቤ ስለ ንጉሡ ብዙ መግለፅ የሚያስችል በመሆኑ፣ እንደ ሌሎች ሁሉ ደብዳቤውን እንዳለ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ አስፍሬዋለሁ:: መስመር በመስመር ላነበበ ሰው፣ ንጉሡ ፈሪሀ*

*እግዚአብሔር እንደነበራቸው፣ ምኞታቸውንና፣ በሀገራቸው ሰዎች ተስፋ የቆረጡ መሆኑን መረዳት ይችላል:: በነበራቸው ኩራት ምክንያት ናፒየርን በመናቅ የደብዳቤው አድራሻ ላይ ስሙን እንኳን አላስገቡትም ነበር:: ይህ ደብዳቤ ማህተም እንኳን የለበትም:: ነገር ግን በአፄ ቴዎድሮስ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ሁሉ በይዘቱ ይህ በጣም ገላጭ ነው::*

## የአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በሶስትነት ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሳ፤ መችም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ሀይል እኔ ካልወረድኩላችሁ ሸሽታችሁን አትተውም:: ክርስቲያኑ ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር እግብቸው፣ ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች፤ ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች፤ ትላንትናም የምተባት ትኖራለች፤ ሽማግሌ፣ ልጅ የሌለው፣ ባልቴት፣ ልጅ የሌላት እኔ የምጠውራቸው ብዙ በከተማየ አሉ:: እግዚአብሔር ከሠጣችሁ ፍቀዷቸው ያረመኔ አገር ነውና:: ያገሬ ሰው ገብር ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ:: እናንተ ግን በስራት(ሥርአት) በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ:: እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ አርባስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ ብትቃቧቸው፤ ከሮጡ ሰዎች ጋራ አልነበርሁም፤ ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ሥታገል ውየ ነው:: ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዟል እስልሟል እያለ እሰሩን ምክንያት ይሠጠኝ ነበረ:: እኔ ከከፋሁበት እግዚዘብሔር መልካም ይሥጠው፤ እንደወደደ ይሁን፤ እግዚአብሔር ቢሠጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ:: ከተወለድሁ አስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ:: ሰዎች ሲሸሹ ተነስቼ ማራጋት(ማረጋጋት) ልማድ ነበረኝ፤ ጨለማ ከለከለኝ:: ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች አግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ:: እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አሰለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር:: ወንድ ያቀፈ ተመልሶ አይታቀፍም::*

*(ባህሩ ዘውዴ፣ ስቨን ሩበንሰን)*